# በማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም3 ላይ በተመረጠው አዲሱ ወረዳ በ2015 በተያዘ ተግባራት ላይ የዘጠኝ ወራት የአፈፃፀም ሪፖርት

## 1. መግቢያ

በኢትዮጲያ መንግስትና በአለም ባንክ መካከል በተደረገ ስምምነት እና ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በማካሄድ ላይ የሚገኘው ሶስተኛውም ዕራፍ የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት በክልላችን ቀደም ብሎ በአራት ወረዳዎች በማካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን።

በክልላችን የማህበራዊ ተጠያቂነት ዑደት ትግበራን በ2015 በጀት ዓመት በአዲሱ ወረዳ ላይ በርካታ ስራዎች ለመስራት እቅድ የተያዘ ሲሆን በ2015 በጀት አመት እስከ መጋቢት ወር 14 ተግባራት ከተያዘው ዕቅድ በመነሳት እስከ መጋቢት ወር ያከናወናቸው 14 ተግባራት ላይ ሙሉ ለሙሉ የተሰራ ሲሆን ይኸውም ክንውን በፐርሰንት 100% ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 2. ዓላማ

- ማህበራዊ ተጠያቂነትን በመንግስት አሰራር ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ እና በሂደትም ተቋማዊ ለማድረግ ነው።
- በ5ቱ መሰረታዊ አገልግሎት ሰጪ ሴክተሮች ላይ አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ነው።

## 3. የሚጠበቅ ውጤት

- ተገልጋይ ህብረተሰቡ የሚፈልገውን እርካታን ይጨምራል፡፡
- ድህነት ይቀንሳል፡፡

## 4. የተሰሩ ስራዎች

- ከገ/ሚ በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት በክልላችን አንድ ወረዳ የማህበራዊ ተጠያቂነት ስራ ተግባራዊ ለማድረግ በተያዘው ፕሮግራም በመነሳት በክልላችን ከቀሩት 5 ወረዳዎች ላይ በማወዳደር አንዱ ወረዳ ለመምረጥ በተቀመጠው መመዘኛዎች መሰረት ሰራው የሚተገበርበትን አንድ የጀኔላ ወረዳ እንዲመረጥ የተደረገ ሲሆን በተመሳሳይም ከወረዳው ጋር በመነጋገር ካሉት 3 ቀበሌዎች አገልግሎት አሰጣጡ ዝቅተኛ ከሚታይባቸው 2 የከተማ ቀበሌዎች ተመርጠዋል፡፡

- የማህበራዊ ተጠያቂነት አሰመልክቶ በጀኔላ ወረዳ ላይ ከህዳር 8–9/2015 ለሁለት ቀናት በተመረጠ ወረዳና 2 ቀበሌዎች ደረጃ በይፋ የስራ ማስጀመሪያ ወርክሾፕ/ Launching Workshop/ ላይ በተያዘው እቅድ መስረት ለ62 ተሳታፊ እቅድ ተይዞ 55 ተሳታፊ በመገኘት በፐርሰንት 88% ሲሆን ይኸውም ወንድ 29 ሴት 26 በመሳተፍ የሴቶች ተሳትፎ 47% ሆነዋል ፡፡

- መሰረታዊ የመንግስት አገልግሎቶች ተገልጋዩን ህብረተሰብ ባሳተፈና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ለማቅረብ እንዲቻል የህዝብን ፍላጎትና የመንግስትን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ለመለየት ከሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶችና ባለድርሻ አካላት ከህዳር 24-25/2015 ለሁለት ቀናት የምክክር ሰብሰባ ላይ ለ40 ተሳታፊ እቅድ ተይዞ 37 ተሳታፊ በመገኘት በፐርሰንት 93% ይኸውም 26 ወንዶች እና 11 ሴቶች በመሳተፍ የሴቶች ተሳትፎ 28% ሆነዋል ፡፡

- በተመረጠው ወረዳ ውሰጥ የሚሰራባቸውን የመሰረታዊ አገልግሎት ደረጃዎች [Basic Service Standard] በሚመለከት ከሚመለከታቸው 5 መ/ቤቶች መረጃ ተሰበሰበዋል፡፡

- በአዲሱ በተመረጠው ጀኔላ ወረዳ ላይ ተቓማዊ ካርታ መረጃ ተሰርቶ በወረዳና እንዲሁም በ2 ቀበሌዎች [ቀበሌ 15 እና ቀበሌ16] ማህበራዊ ተጠያቂነት መድረኮች [WSAP] በወረዳ 15 የያዘ አባላት እንዲሁም በቀበሌዎች ለእያንዳንዱ 11 አባላት የያዘ ሲሆን ሰብጥሩም ከተለያዩ አካላት እንዲዋቀር ሆነዋል ::

- ሰራው ለሚመለከታቸው የመንግስት ባለድርሻ አካላት ማለትም ለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት፣ ለተመረጡ ሴክተር ሃላፊዎች ፣ ለጉዳት ተጋላጭ ማህብረተሰብ ፣የቡዙሃን ማህበራት ተወካዮች፣ ተዋቂ የማህበረተሰብ ምስረታ ተቓማትና እንዲሁም የወረዳና የቀበሌ የማህበራዊ ተጠያቂነት መድረክ ሰብሳቢና ፀሃፊ ጭምር በማህበራዊ ተጠያቂነት በትግበራ መመሪያ ላይ ከታህሳስ 7-8/2015 ለሁለት ቀናት ግንዛቤ ማሰጨበጫና አቅም ግንባታ ስልጠና ለ40 ተሳታፊ እቅድ ተይዞ 35 ተሳታፊ በመገኘት በፐርሰንት 88% ሲሆን ይኸውም 24 ወንዶች እና 11 ሴቶች በመሳተፍ የሴቶች ተሳትፎ 31% ሆነዋል ::

- በተመረጡ አገ/ መሰጫ ተቓማት ከቀበሌው ማህበራዊ ተጠያቂነት መድረክ ጋር በመሆን በሁለት ቀበሌዎች ሰድስት የውይይት ቡድኖችን በአንድ ቡድን አሰራ አምስት አባላት በጠቅላላው ዘጠና አባላቶች በሁለቱ ቀበሌ ተቓቁመዋል::

- ለተዋቀረው መድረክ አባላት ለወደፊቱ ለሰራው ለሚያስፈልጋቸው የፅ/መሳሪያዎች ማለትም ማስታወሻ ደብተር፣ እስክሪቢቶ፣ የቃለጉባኤ መዝገብ፣ ፋይል አቃፊ፣ ፍላሽ እንዲሁም ሌሎች የፅ/መሳሪያዎች እንዲገዛላቸው በማድረግ ለአባላቶቹ እንዲሰራጭ የተደረገ ሲሆን ለአመቻቾችም ለግምገማ ስራ ፍሊፕ ቻርት እና ፓርከር እንዲገዛ ተደረገዋል::

- የማህበራዊ ተጠያቂነት የጋራ ውይይቶች አመቻቾችን በሰራው ልምድ ካላቸው IPs አካላት ጋር በመተባበር ከታህሳስ 18-19 ለሁለት ቀናት ግንዛቤ ማሰጨበጫና አቅም ግንባታ ስልጠና ለ23 ተሳታፊ እቅድ ተይዞ 23 ተሳታፊ በመገኘት በፐርሰንት 100% ሲሆን ይኸውም 15 ወንዶች እና 8 ሴቶች በመሳተፍ የሴቶች ተሳትፎ 35% ሆነዋል ::

- ለትኩረት ቡድኖች ሰለማህበራዊ ተጠያቂነት ምንነትና ሰለማህበረተሰብ መመዘኛ ካርድ አሰራር ስልጠና በሁለት ዙር ለሁለት ቀናት የግንዛቤ ማሰጨበጫና አቅም

ግንባታ ስልጠና ለ117 ተሳታፊ እቅድ ተይዞ 105 ተሳታፊ በመገኘት በፐርሰንት 90% ሲሆን ይኸውም 45 ወንዶች እና 60 ሴቶች በመሳተፍ የሴቶች ተሳትፎ 75% ሆነዋል።

- በአዲሱ ወረዳ ላይ የማህበረተሰብ መመዘኛ ካርድ በመጠቀም ለሚካሄደው የአገልግሎት ግምገማ ስራ ከመካሄዱ በፊት በ2 ት/ቤቶች ላይ የወረዳና የቀበሌ ማህበራዊ ተጠያቂነት መድረክ ሰብሳቢና በትኩረት ቡድኑ የተመረጡት አመቻቾች ባሉበት ጥር23/2015 ላይ የመሰክ ጉብኝት ተካሂደዋል።

- በማህበረሰብ መመዘኛ ካርድ በመጠቀም በ2 ቀበሌዎች ላይ የትኩረት ቡድኑ አገልግሎቶች ላይ ግምገማ ለማድረግ ከየካቲት 22-23 ለሁለት ቀናት ለ 120 አባላት ግምገማ እንዲያደረጉ ተይዞ 110 አባላት በመገኘት በፐርሰንት 92% ሲሆን ይኸውም 50 ወንዶች እና 60 ሴቶች በመሳተፍ የሴቶች ተሳትፎ 60% ሆነዋል ።

- በጀንኤላ ወረዳ በተገልጋይ ህብረተሰብ እና የአገ/ሰጪዎች በማህበረተሰብ አገልጋይ መመዘኛ ካርድ/Community Score Card/ አማካኝነት የተገመገመውን ውጤት ገፀ-ለገፀ /Interface Meeting/ ውይይት ለማድረግ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ የሚፈታውን ችግሮችን በመለየት ሶስት መድረክ በማዘጋጀት በጠቅላላው ለ112 አባላት ውይይት ለማድረግ ተይዞ 108 አባላት በመገኘት በፐርስንት 96% ሲሆን ይኸውም 65 ወንዶች እና 43 ሴቶች በማሳተፍ የሴቶች ተሳትፎ 40% ሆነዋል

## 5 የተገኘ ጠንካራ ጎን

- በተመረጠው ወረዳ ላይ የወረዳው አመራሮች ለማህበራዊ ተጠያቂነት ለሚከናወኑ ስራዎች በወረዳው በኩል ፈጣን ምላሽ መስጠታቸውና ለማህበራዊ ተጠያቂነት ስራ በወረዳው በኩል ከፍተኛ ተነሳሽነት መፈጠሩ።

- በቀበሌዎች ያሉት የማህበራዊ ተጠያቂነት መድረክ አባላት በተሰጣቸው ስልጠና መሰረት በእቅዳቸው መሰረት በቀበሌ ውስጥ ለሚደረገው ማንኛውም ሰብሰባ ላይ በቀበሌ ውስጥ ለሚኖሩት ማህበረሰብ ሰለማህበራዊ ተጠያቂነት ግንዛቤ መስጠት መጀመሩና እንዲሁም በወረዳ ያሉት የማህበራዊ ተጠያቂነት መድረክ አባላት

በእቅዳቸው መሰረት ስለተደረገው እንቅስቃሴ በተሰጣቸው መዝገብ ላይ ቃለጉባዬ መያዝ መጀመሩ ፡፡

- ለወረዳው ለሰራው የሚያስፈልጉትን እስትሽነሪ ለማህበራዊ ተጠያቂነት መድረክ አባላት የተሰራጨ ሲሆን ይኸውም መረጃዎችን በሰርአት መያዝ ተችለዋል፡፡
- ለተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች ማህበራት ተወካዮች በሚሰጠው ስልጠና ላይ በመሰረታዊ አገልግሎት ደረጃዎች ላይ በ4ቱም የድህነት ተኮር ዘርፎች የሚገኙት ባለሙያዎች ለህብረተሰቡ ማህበራት ተወካዮች ገለፃ እንዲደረግላቸው መድረክ ተመቻችቶላቸው ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርገዋል፡፡
- በማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ላይ የሚሰሩት ሰራዎች ህብረተሰቡ ስለ ፕሮግራሙ መረጃ እንዲኖረው በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በተከፈተው ድህረ ገፅ መረጃዎች የሚሰራጩ መሆኑን፡፡

## 6. ያጋጠሙ ችግሮችና የተደረገው መፍትሄ

- በአዲሱ በተመረጠው ወረዳ ላይ የተደራጅ ህዝባዊ ማህበራት ተወካዮች በተሟላ መልኩ በወረዳው ውሰጥ አለመኖር ችግር ቢያጋጥምም ከሚመለከተው ጋር በመነጋገር ለወደፊቱ ለማደራጀት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ስራውን ለማካሔድ የተሸከርካሪ እጥረት ቢኖርም በአለው ተሸከርካሪ ከሌላ ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራ ተደርገዋል፡፡
- የተገልጋይ ህብረተሰብ እና የአገ/ሰጪዎች በማህበረተሰብ አገልጋይ መመዘኛ ካርድ በመጠቀም የተገኘውን ውጤት በገፀ-ለገፀ ውይይት በማድረግ የጋራ እቅድ ለማዘጋጀት ከሚመለከታቸው ከቢሮ ተወካይ ጋር የሚደረግ ቢሆንም በስተመጨረሻ ለሚደረገው የጋራ ድርጊት መርሃ-ግብሩ ላይ ከቢሮ ሃላፊዎች ጋር ለመፈራረም ለስራው ውጣውረድ/ምልልስ/ ያለው ቢሆንም ከቡዙ ወጣ ውረድ ችግሩ ሊቀረፍ የተቻለ ሲሆን በመጨረሻም በገፀ-ለገፀ ውይይት ላይ የመ/ቤቱ ሃላፊዎች መገኘት እንዳለባቸው ትምህርት ወሰደንበታል፡፡

## 7 የወደፊት ትኩረት አቅጣጫ [ቀጣይ የሰራ ፕሮግራም]

- የጋራ እቅድ መርሃግብር/Joint Action Plan/ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ማሰራጨትና በ2016 በጀት አመት በእቅዱና በበጀት ስለመያዙ ክትትል ማድረግ፡፡

- በተያዘው የጋራ እቅድ ላይ ከማህበራዊ ተጠያቂነት መድረክ አባላት ጋር በመሆን በየወቅቱ እቅዱ ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትል በማድረግና የተደረገውንም የክትትል ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፡፡